# የሴናተሮቹ የአዲስ ዓመት ገፀበረከት

መለስ ዓ.

ሴናተር ረስ ፋይንጎልድ ከዊስክንሲን ግዛት የተወከሉ ሴናተር ናቸው። 20 ዓመታት በዘለቀው የፖለቲካ ህይወታቸው በርካታ በግዛቲቱ ጠቀሜታ ያላቸው ህጎች(ቢል) ለሴኔቱ በማቅረብ ይታወቃሉ። ፋይንጎልድ በቡሽ አስተዳደር ወቅት የኢራቅና አፍጋኒስታን ጦርነትን በመቃወም አሜሪካ ወታደሮቿን እንዳትልክ ሲወተውቱ ነበር። ሴናተሩ ባለፈው ግንቦት ወር ለሴኔቱ ከወራት በኋላ ለሚመረጡ የኮንግረስ አባላት የክፍያ ጭማሪ እንድደረግ የሚጠይቅ ቢል በማቅረብ ድጋፍን አግኝተዋል።

ሴናተሩ ሐምሌ 29/2002 ደግሞ አሜሪካ ኢትዮጵያን በተመለከተ አዲስ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን እንድትከተል የሚጠይቅ ህግ በእንግሊዘኛ "Support for Democracy and Human Rights in Ethiopia Act 2010" ለሴኔቱ አቅርበዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ ረቡዕ ነሐሴ 26/2002 ዓ.ም፣ የማነ ናግሽ የተባሉ ፀሃፊ ያቀረቡትን ዘገባ በጥሞና ተመልክቼዋለሁ። በመጀመሪያ ፀሃፊው በዚሁ ጋዜጣ ላይ በተለያዩ ርዕሶች የሚያቀርቧቸውን ፅሁፎች የምከታተል መሆኔን እና ለዚሁም አድናቆቴ ከፍ ያለ መሆኑን በትህትና መግለፅ እፈልጋለሁ። ከዚህ በተጨማሪም በረቂቅ ሕጉ ላይ አንዳንድ አስተያየት መስጠታቸውም ተገቢ ነው። ይሁን እንጂ በዘገባቸው ላይ አንዳንድ እርማቶችን እንዲያደርጉ እጠይቃለሁ። በመጀመሪያ ኤች-አር 2003 የተረቀቀው በህግ መምሪያው እንጂ በህግ መወሰኛ ምክር ቤቱ አልነበረም። ከዚህ በተጨማሪም የዘንድሮው ህግ ለአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቀርቧል የሚለውም የተሳሳተ አስተያየት ነው። አዲሱ ህግ የቀረበው በሴኔቱ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ነው። ፅሁፉን ሲጀምሩ የአሁኑ ህግ ኤች-አር 2003ን ይተካል የሚል መነሻ ይዘው ከቆዩ በኋላ ህጉ ከአሁኑ ጠንክር ይላል የሚል አስተያየት እንዳላቸው መገለፁ እርስ በርሱ የሚጣረስ ሃሳብ ነው የሚል አስተያየት አለኝ። ዋናው ቁምነገር ግን የአሁኑ ህግ ከ2002 ዓ.ም. ምርጫ፣ የበጎ አድራጎትና ፀረ-ሽብርተኝነት ህግ፣ የወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ይቅርታ መነሳት አልያም የኢትዮ-ኤርትራ ድንበር ጋር የሚያይዘው አንድም ቀጥተኛም ሆነ ሌላ ምክንያት የለም።

ዛሬ ስላለንበት ለመናገርም ሆነ ለመፃፍ ትናንትን ማንሳት የግድ ሆነብኝና በ1997 ዓ.ም. በአገራችን ውስጥ በተካሄደው ምርጫ ዋዜማ የወጣውን ኤች. አር. 2003 ህግ አስታወስኩ። ዘንድሮም ሌላ ህግ ለ2003 ዓ.ም. በገፀ-በረከትነት ቀርቦልናል። እነዚህ ህጎች የበፊቱ ኮንግረስማን ዶናልድ ፔይን ክሪስ ስሚዝና ማይክል ሆንዳ ከመቅረቡ፡ የአሁኑ ደግሞ በዋነኛነት በሴናተር ረስ ፋይንጎልድ አዘጋጅነት እንዲሁም በሴናተር ፓትሪክ

ሌሃይ ድጋፍ ከመቅረቡ ውጭ በይዘት ብቻ ሳይሆን በቃላት ሳይቀር ተመሳሳይ ናቸው:: ሁለቱንም ሀሜትና ክስ በጋራ ይገልጻቸዋል:: የአሁኑንም ካለፈው ጋር የሚያመሳስለው ጉዳይ ቢኖር የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታዎች በምንም መልኩ አለማንፀባረቁ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያን ፓርላማ አስቀምጠን ለኢትዮጵያውያን ህግ እናውጣ የሚል ንቀት የተላበሱ ናቸው:: እርግጥ ድሃ ነን:: ግን ለእነርሱ እኛም ህግ እንድናወጣላቸው ይፈቅዱልን ይሆን ? እንዲህ ከሆነ ከኒውዮርክ የአልቃይዳ ጥቃት በኋላ የወጣው አወዛጋቢው የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ /Patriotic Act/ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን የሚጋፋ ነውና እንዲሻሻል እናሳስባ!! አለበለዚያ..... ::

አዲስ የወጣው ረቂቅ ውሃ ይቋጥራል ? አሊያም በኢትዮጵያ ላይ በሚኖረው እንድምታ ላይ አስተያየት ከመስጠቴ በፊት ሴኔተር ፋይንጎልድና ሌሎች መሰሎቻቸው የሚዘነጉት የኢትዮጵያ ህዝቦችን ስነልቦናና ባህሪይ/Ethiopian Personality Traits/ ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያየ ወቅት ጥሩም መጥፎም መንግስታት ነበሩ:: ሁሉንም የሚያመሳስላቸው ደግሞ ክፉ ድህነት ውስጥ እንኳ ሆነን ብሔራዊ ክብራችንን ለጨረታ አለማቅረባቸው ነው:: ይህ የኢትዮጵያዊነት ስብዕና በዓድዋ ጦርነት 1896፣ በፋሽስት ጣሊን ወረራ ወቅት 1933፣ እንዲሁም ኢህአዴግ ገና ስልጣን እንደያዘ 1983 ሆነ ዛሬም ያለ ነው:: ስለሆነም ለዲሞክራሲ ሥርዓት አዲስ ብንሆንም ወድቀን እየተነሳን የተሻለች ኢትዮጵን እንፈጥራለን:: ሞግዚት ግን አንፈልግም:: ይህ የሃያላኑ አገር ሴኔተሮችና ም/ቤት አባላት እጅ የመጠምዘዝ አባዜ ሌላ ቦታ ሊሰራ ይችላል:: ለሁሉም አገሮች አንድ አይነት የማይሰፋ የማይጠብ የብረት ጃኬት /Metal Jacket/ ውስጥ እንድንገባ ሊደፍቁን ሲሞክሩ እምቢኝ የማለታችን ሚስጥሩ ይኸው ነው::

ኤች .አር. 2003ም የሃርቫርዱ ዶክተር ሴናተር ረስ ፋንጎልድ ያወጧቸው ህጎች ላይ ላያቸውን ለተመለከተ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እንዲሰፍን ስለሚፈልገው ሠላም፣ ዲሞክራሲ፣ የሰብዓዊ መብት መከበር ወዘተ... የሚያወሩ ይምሰል እንጂ ወርቁ ሌላ ነው:: ያለፈውን ህግ ትተን እስኪ ሴኔተር ፋይንጎልድ ያቀረቡትን ህግ 2010 ዋና ዋና ናቸው የምንላቸውን ጭብጦች እንመልከት::

ህጉ አሳታፊ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት እንዲኖር፣ ያልተገደበ የሲቪል ማሕበረሰብ እንቅስቃሴ እንዲኖር፣ አሸባሪነትን ከዓለም አቀፍ ህግ ጋር በሚጣጣም መልኩ መዋጋት እንዲቻልና ለኢትዮጵያ የፀጥታ ኃይሎች ከአሜሪካ የሚሰጠው ድጋፍ እንዲቆም ይጠይቃል:: በመቀጠልም የኢትዮጵያ መንግስት ከላይ በተጠቀሱትና ሌሎች ጉዳዮች ላይ የሚታዩ እርምጃዎች መውሰዱን የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ለኮንግረስ

ካላረጋገጠ በስተቀር ለኢትዮጵያ መንግስት ድጋፍ እንዳይደረግ ይጠይቃል:: ይህ እቀባ ግን አሜሪካ በኤች. አይ. ቪ /ኤድስ መከላከልና የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታን እንደማያጠቃልል ይገልፃል::

የመጀመሪያው ኢትዮጵያ በታሪኳ አራተኛውን ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ በማካሄድ ህዝቡ ይሁንታውን ከነችግሮቹ ለገዢው ፓርቲ ከሰጠ ሰንብቷል:: ታዲያ የት ከርመው ነው ዘሬ ስለምርጫ የማሚክሩን? ምናልባት የአውሮፓ ህብረት ታዛቢ ቡድን በቅርቡ በምርጫው ላይ ከሚያወጣው የመጨረሻ ሪፖርት ጋር እንዲጣጣም በማድረግ ቀደም ሲል ተጀምሮ የነበረው ቀጣዩን መንግስት ህጋዊነት የማሳጣት ዘመቻ ለመቀጠል ከሆነ ጊዜው አልፎበታል:: ይህን የሚያራግበው ፅንፈኛ የዳያስፖራ ቡድንም ሳስቷል:: ለዓመታት ተደፍቆ የኖረው ዝምተኛው ዳያስፖራ ይህን የተሳሳተ አቅጣጫ በፅኑ ይቃወመዋል የሚል ሙሉ እምነት አለኝ:: ሁለተኛው ከፋም ለማም ኢትዮጵያውያን የራሳችንን ህግ የማውጣት መብት አለን:: ለአገራችን የልማት ጥረት አስተዋፅዖ የሌላቸው የሻንጣ ውስጥ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና በራሳችን የውስጥ ጉዳይ ወሳኝ መሆን የሚፈልጉ ግልፅ አሰራርና ኃላፊነት የሚሰማቸውን መለየት የኢትዮጵያ መንግስት ስልጣን ነው:: ኢትዮጵያ የአሸባሪዎች ጥቃት ዒላማ የሆነችው አልቃዒዳዎች ኒውዮርክ ውስጥ የህዝብ አውሮፕላን እንደ ጦር መሣሪያ ተጠቅመው ንፁሃንን ከፈጁ በኋላ አይደለም:: ኢትዮጵያ ይህን እኩይ ተግባር የሚገታ የፀረ-ሽብር ህግ ማውጣቷን ሴኔተሩ መኮነን ለምን ይፈልጋሉ ? የአሜሪካ ኮንግረስ ለፌዴራሉ መንግስት ሰፊ ሥልጣን የሚሰጥ ህግ /Patriotic Act / በሚል ቅፅል ሲያወጣ የተለያዩ ሲቪል ማህበራት ተቋማት በፅኑ ቢኮንኑትም ተግባራዊ ሆኗል:: የአሜሪካ ሲቪል መብቶች ህብረት /American Civil Rights Union/ ህጉ የአገሪቱን ህገ-መንግስት የሚጥስ ነው በሚል በፅኑ ቢቃወምም ሰሚ አልነበረውም:: ይህ ህግ ኤፍ.ቢ.አይን ለመሳሰሉ የስለላ ተቋማት እና የአቃቤ ሕግ አካላት ሰፊ ስልጣን የሚሰጥ ነው:: በዚህ ህግ መሠረት የግለሰቦች የስልክ መስመር መጥለፍ፣ የባንክ ሂሳባቸውን መፈተሽ፣ የህክምና ሪኮርዳቸውንና የጉዞ ሰነዶቻቸውን ያለባለቤቶቹ ፍቃድ መበርበር በሕግ የተፈቀደ ነው::

የሴናተር ፋይንጎልድ ረቂቅ ሕግ ለኢትዮጵያ የፀጥታ ኃይሎችከኣሜሪካ የሚሰጠው ድጋፍ እንዲቆም ያዛል:: ለመሆኑ ከአሜሪካ ምን አይነት የጦር መሣሪያ እናገኛለን? በፀጥታ ጉዳይ ከአሜሪካ ጋር የሚደረገው ትብብርስ ምን ይመስላል? የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ከአሜሪካ ኤፍ-16 የጦር አውሮፕላን ወይስ አፓቼ ሔሊኮፕተር ነው የሚያገኘው? አይመስለኝም:: በዓላማ የታነፀና እና ዲሲፕሊንድ የሆነው የመከላከያ

ሠራዊታችን ከአሜሪካን ይልቅ የሌሎች አገሮችን የጦር መሣሪያዎች እንደታጠቀ መገመት ይቻላል:: የመከላከያ ኃይላችን ዛሬ የጦር አውሮፕላንና ሔሊኮፕተሮችን ለጥገና ይዞ ሌላ አገር የሚይኳትን መሆኑን በአንድ ወቅት በተዘጋጀ ኤግዚቢሽን ስመለከት ኮርቼበታለሁ:: ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አገራችን የሶማሊያ አሸባሪዎችን ለመምታት ከአሜሪካ የምታገኘው የጦር መሣሪያና ሌላ ድጋፍን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ "መቼም በኮንዶም አንዋጋ" ሲሉ ከአሜሪካ የሚገኘው በአብዛኛው ለኤች. አይ. ቪ ኤድስ ድጋፍ አስመልክቶ የሰጡት መልስ ለሴኔተር ፋይን ጎልድም ይሰራል::

ሴናተር ፋይንጎልድ ያቀረቡት ረቂቅ ህግ በመጨረሻ ተቀባይነት አግኝቶ ተግባራዊ ቢሆን የሚጣለው የፋይናንስ ማዕቀብ የኤች .አይ. ቪ/ኤድስ መከላከልንና የአስቸኳይ ጊዜ የሰብዓዊ ዕርዳታን እንደማያካትት ቃል ይገባል:: ሴናተሩ ይህን ሲሉ አሜሪካ ለኢትዮጵያ ከእነዚህ ጉዳዮች ውጪ የምትሰጠው ቤሳቤስቲን እንደሌላት ዘንግተው አይደለም:: የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለፃ አሜሪካ በያዝነው አውሮፓውያን አቆጣጠር 533 ሚሊዮን ዶላር እርዳታ ለኢትዮጵያ ስትሰጥ ከዚህም ውስጥ 411 ሚሊዮን ዶላር የሚሆነው ኤች. አይ. ቪን ጨምሮ ለጤናና ለአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ የሚውል ነው:: በቀላል አነጋገር ገንዘቡ በአንድ የአሜሪካ ግዛት የሚገኝ የኮንዶም ፋብሪካ ያመረተውን ኮንዶም ለመግዛትና ስለአጠቃቀሙ የተዘጋጀውን በራሪ ወረቀት ለማስተማር ወደአገራችን የሚመጡ ቀለም በወጉ ያልቆጠሩ አሜሪካውያን የሚቀራመቱት እንጂ ለኢትዮጵያ በቀጥታ የሚሰጥ ዶላር አይደለም:: ስንዴውም ያው እንደዚያው ነው:: አንድ ኩንታል ስንዴ ከአሜሪካ 250 ዶላር (በእኛ ገንዘብ መንዝሮ ማስላቱ አግባብ ይሆናል) ተከፍሎበት የሚመጣ ይህም አብዛኛው ገንዘብ እዚያው እንደሚቀር ማሳያ ነው:: ስለሆነም የሴናተር ፋይንጎልድ ክስ እንዲሁም ረቂቅ ህግ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ምንም መሠረታዊ ግንኙነት የላቸውም:: ካለፈው ምርጫ በኋላ የተለያዩ ህጎች መውጣት ጋር በጊዜና ቦታ ምንም የተገጣጠሙ አይደሉም::

<u>የሲማሊሞ ዲፕሎማሲ</u>

የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ በቅርቡ በሱዳን ልዩ ልዑክ ያደረጓቸው ፕሪንስተን ሌይማን የአሜሪካ ኮንግረስ የውጭ ግንኙነትና የግሎባል ጤና ጉዳዮች ኮሚቴ ያዘጋጀው መድረክ ላይ ያደረጉት ንግግር የብዙ ፀረ-ኢትዮጵያ ወገኖችን እንጥል የቀረጠ ነበር::

ተመራማሪው አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ ተፅዕኖ ለማሳረፍ ፖለቲካዊ አቅም (Political Leverage) የላትም ብለዋል፡፡

ፕሪንስተን ሊይማን እና ስቴፈን ቢድል የተባሉ የውጭ ግንኙነት ምክር ቤት የተባለ ተቋም ተባባሪ ተመራማሪ ጋር ባቀረቡት ፅሁፍ አሜሪካ ለሰብዓዊ እንዲሁም ነፍስ አድን የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ መከላከል የምታደርገውን ዕርዳታ በከፍተኛ ሁኔታ ብትጨምርም ዋሽንግተን በምትረዳቸው ወገኖች ላይ ተፅዕኖ ማሳረፍ አልቻለችም በማለት ገልፀዋል፡፡ ሁለቱም ተመራማሪዎች እዚህ ላይ በአብነት የጠቀሱት አንዷ ከሰሃራ በታች ያለች አገር ኢትዮጵያ ናት፡፡ ይህን ሃቅ ሴናተር ፋይንጎልድም የሚያጡት አይመስለኝም፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሂላሪ ክሊንተን ይህን አካሄድ በመለወጥ ልማትና ዲፕሎማሲን በአንድነት ተጠቅሞ የመሄድ ፍላጎት አላቸው እየተባለ ቢሆንም ልማት የረጅም ጊዜ ዲፕሎማሲን ደግሞ ለአስቸኳይ ሁኔታ የሚውል ስለሆነ አይሳካላቸውም እየተባለ ነው፡፡

በፋይንጎልድ የቀረበው አዲስ ረቂቅ ህግ ሁሉም ሴኔተሮች ከራሳቸው ደጋፊ (Constituency) አንፃር እና ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለውይይት የሚያቀርቧቸው የተለመዱ ሥራዎች መሆናቸውን መገንዘብ ይገባል፡፡ ሴኔት ይህን አይነት ረቂቅ ህግ ቀርቦለት ካላየ ታዲያ ምን ይሰራል፡፡ በሴኔቱ የውጭ ጉዳይ ንዑስ ኮሚቴ ሊቀመንበር ጆን ኬሪ እና በተዋረድ ታይቶ ለመፅደቅ ረጅም ጊዜ የሚፈጅበት ሁኔታ እንዳለ ሆኖ ረቂቅ ህጉ ተግባራዊ እንዲሆን በባራክ ኦባማ ይፈረማል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ህጉ ተግባራዊ ቢሆን ከኢትዮጵያ ይልቅ የአሜሪካንን አስተዳደር ይጎዳል፡፡ ምክንያቱም በአፍሪካ ቀንድ የአሜሪካ መንግስት ብሔራዊ ጥቅሙን ለማስከበር በሚያደርገው ጥረት ኢትዮጵያ መልህቃዊ ሚና ያላት አገር(Anchor State) ናትና በዚህ ቢል ጉዳይ አይደራደርም፡፡ በአፍሪካ ቀንድ ሶማሊያ ያው ሶማሊያ ናት፡፡ ሱዳንም ዕጣ ፈንታዋ አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ ነው፡፡ ጂቡቲም እንደዚያው ጂቡቲ ናት፡፡ ኬንያም በአካባቢው ካለፈው ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ በኋላ የሰላም ተምሳሌትነቷ ተረት ተረት ሆኗል፡፡ ኤርትራም የአልቃይዳ ደንገጡር ናት፡፡ ስለሆነም ለጊዜውም ይሁን አይሁን በክልሉ የኢትዮጵያ ሚና አይተካም፡፡ እዚህ ላይ የማይካደው ጉዳይ ህጉ ቢወጣ የሁለቱን አገሮች ግንኙነት የሚያሻክረው ይሆናል፡፡ እንደዚህ አይነት ሂሳብ ለማወራረድ የሚያስችል ሁኔታ በአሁኑ ወቅት እንደሌለ አሜሪካውያን አይጠፋቸውም፡፡

ኃያላኖቹ አገሮች በኢህአዴግ የሚመራውን የኢትዮጵያ መንግስት በተለያየ ወቅት እጁን ለመጠምዘዝ ሞክረው አልተሳካላቸውም፡፡ ከዛሬ 19 ዓመት በፊት ገና በጨቅላ ዕድሜው ቴሌን ሽጥ በርህን ለውጭ ባንክ ክፈት ተብሎ አሻፈረኝ ነው ያላቸው፡፡ በኤርትራ

በተወረርን ጊዜ ታሪክን ደግመው ወራሪና ተወራሪ ላይ እኩል ማዕቀብ ጥለዋል፡፡ ከ1997 ምርጫ በኋላም የሚሰጡትን የልማት ዕርዳታ ማስፈራሪያ ሊያደርጉት ቢሞክሩም የመንግስት አቋም የፀና ነው፡፡ ሰጥቶ በመቀበል መርህ መደራደር አንድ ነገር ነው፡፡ አላስፈላጊ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ከሆነ ግን በሊማሊሞ አቋርጠው መሄድ መብታቸው ነበር፡፡

<u>**ጉድና ጅራት...**</u>

ሴኔተር ፋይንጎልድ ያቀረቡት ቢል አገራችን የጀመረችውን የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ፣ የመልካም አስተዳደርና የልማት ጥረት የመደገፍ ዓላማ ቢኖረው እሰየው የሚያሰኝ እንደሆነ ቀደም ሲል ለመግለፅ ሞክሬያለሁ፡፡ በተለያየ ወቅት አሥመራ ባቀኑበት ወቅት ከኢትዮጵያ ይልቅ ከፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ በላይ መንግስትም ህገመንግስትም ከሌላት ኤርትራ ጋር ተግባብቶ መሥራት ያቻላል የሚል እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ ባቀረቡት ሕግ ላይ ቢሉ ሚዛናዊ ነው የሚል መልዕክት እንዲኖረው ኤርትራን አገም ጠቀም ባለ መልኩ ለማንሳት ሞክረዋል፡፡ ሴናተሩ ኢትዮጵያ የኢትዮ-ኤርትራን የድንበር ውሳኔ ትቀበል ሲሉ ጥሪ ያቀርባሉ፡፡ ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውሳኔውን ከዛሬ ስድስት ዓመት በፊት በመሠረተ ሃሳብ ደረጃ መቀበሏን አስታውቃ የለም እንዴ? በዓለም አቀፍ ልምድ መሠረት ቁጭ ብለው ሳይነጋገሩ እንዴት መሬት ማካለል ይቻላል? ሴኔተሩ የአስመራ መንግስት ወዳጅ በመሆናቸው ይህን እንዳይሉ መጠበቅ አይገባም፡፡ የኤርትራ መንግስት የተባበሩት መንግስታት የሰላም አስከባሪ ኃይልንም አባሯል ብለው ህጉ ላይ ሳይጠቅሱት ለምን አለፉ ?

ሴኔተር ፋይንጎልድ ያቀረቡት ቢል ከወቅታዊው የኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር የሚያገናኘው አንደም ክር የለም፡፡ የሴኔተሩ ክስ ማጠንጠኛ የወደፊቱን የፖለቲካ ህይወታቸውን የሚወስነውና እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 2/2010 የሚካሄደው ምርጫ (Mid Term Election) ጉዳይ ነው፡፡ ከሴኔቱ 100 መቀመጫዎች ውስጥ ለ37 ምርጫ ከሚካሄድባቸው የአሜሪካ ግዛቶች አንዷ ሴናተሩ የሚወዳደሩባት ዊስኮንሲን ዋና ናት፡፡ ማርክ ሃልፐሪን የተባሉ ፀሃፊ ሰሞኑን ታትሞ በወጣው ታይም መፅሔት ላይ እንዳሰፈሩት ከአፍጋኒስታን ጦርነት መንተት፣ ከመካከለኛው ምስራቅ ድርድር ውጤት አልባነት እንዲሁም ኦባማ ኒውዮርክ ውስጥ ግራውንድ ዜሮ አጠገብ መስጊድ እንዲሰራ ከመፍቀዳቸው ጋር ተያይዞ እየቀረበባቸው ያለው ወቀሳ ፓርቲው በቅርቡ በሚካሄደው ምርጫ ላይ ሽንፈት እንዲገጥመው ሁኔታዎችን አመቻችቷል፡፡ ለዚህም ዲሞክራቶች ማሳቹሴትስ ውስጥ በቴድ ኬኔዲ አማካኝነት ለ50 ዓመታት ይዘውት የነበረውን ሴኔት መቀመጫ

ማጣታቸው ለዲሞክራቶች የማስጠንቀቂያ ደውል ነው፡፡ ፀሃፊው እንደሚሉት ሪፐብሊካኖች በቀጣይ ዋሽንግተንና ዊስኮንሲን ውስጥ የድል ችቦ ያበራሉ፡፡ በዚህ ግምት መሠረት ረቂቅ ህጉን በኢትዮጵያ ላይ ያቀረቡት የዲሞክራቲክ ፓርቲ ዕጩ ሴኔተር ፋይንጎልድ ለ20 ዓመታት ያለምንም ስጋት ቢቆዩም አሁን ግን ፈታኝ ፉክክር ይጠብቃቸዋል፡፡ ከሴኔተር ፋይንጎልድ ጋር አንገት ለአንገት እየተተናነቁ ያለት የሪፐብሊካኑ ዕጩ ቱጃሩ ሮን ጆንሰን ናቸው፡፡ ሚስተር ሮን ጆንሰን ለዚሁ ምርጫ ከሴኔተር ፋይንጎልድ ሶስት እጥፍ ያህል ገንዘብ በማውጣት ለመመረጥ እየተፎካከሩ ሲሆን ሴኔተር ፋይንጎልድን ጨምሮ ሌሎች የዲሞክራት ፓርቲ እጩዎች የመሸነፉ እድል አላቸው፡፡ ኒውዮርክ ታይምስ ነሐሴ 27 ቀን 2002 ዓ.ም. እንደዘገበው ሪፐብሊካኖች ከጠበቁት በላይ ድል ያገኛሉ፡፡ በዚህም በሴኔቱ የበላይነታቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ ስለዚህ ሴኔተር ፋይንጎልድ ይህችን መራር ፅዋ ላለመጎንጨት የማምለጫ አማራጭ ያደረጉት ኢትዮጵያን መክሰስ ነው፡፡ ይህ ቢል የወጣበት ዋነኛ እንዲያውም ብቸኛ ምክኒያት ይኸው ነው፡፡ ይህ ድርጊታቸው አንድ የኦሮሚኛ አባባልን ያስታውሰኛ ል፡፡ ጠፍቶ የማያገኙትን ግመል ለሰበብ ማሰሮ ውስጥ ይፈልጉታል የሚል፡፡ ይህ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት በምርጫው ወቅት የኢትዮ-አሜሪካውንን ድጋፍ ለማግኘት ነው እንዳይባል ዊስኮንሲን ኢትዮጵያውያን በብዛት ከሚኖሩባቸው ዋሽንግተን፣ ሎሳንጀለስ ወይም አትላንታ ከተሞች ጋር የምትወዳደር አይደለችም፡፡ ምናልባት የካሊፎርኒያው ሪፐብሊካን ኮንግረስ ማይክ ሆንዳ ቢሆኑ መላምቱ በሰራ፡፡ ግን የሴኔተር ፋይንጎልድ ጉዳይ ሌላ ነው፡፡

**<u>ይበቃል!</u>**

አሜሪካ በቀጥታ የመንግስት መዋቅሮች አማካኝነት አመለካከቷን ለመጫን ከምታደርገው ጥረት በተጨማሪ ሌሎች መደበኛ ላልሆኑ መንገዶች ድጋፍ በማድረግ እምቢ ያሉትንም በመቆንጠጥ (Carrot and Stick) የኒዮሊበራል አመለካከት አራማጅ እንዲሁም ለዋሽንግተን ኮንሰንሰስ ተገዢ የሆኑ አገራት እንዲኖሩ ትሰራለች፡፡

በአፍሪካ በነዳጅ ዘይትና የተለያዩ የተፈጥሮ ሃብታቸው ሃብታም የሆኑ አካባቢዎች ውስጥ የሚፈጠሩ መጠነኛ መፈናቀሎችን በማራገብ የከፋ አደጋ እንዲደርስ ካደረጉት ውስጥ የአሜሪካ የዕድገት ማዕከል (Center for American Progress) ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ ድርጅት በሱዳን ዳርፉር ውስጥ ተነስቶ የነበረው ጦርነት እንዲባባስ አድርጓል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ከሴኔተር ፋይንጎልድ ጋር ምን አገናኛቸው የሚል ጥያቄ የሚያጭር ነው፡፡ ሴኔተር ፋይንጎልድ በዚህ የኢነፍ(Enough) ፕሮጀክት አባል ሲሆኑ ለሴኔት ባቀረቡት ህግ

ላይ በሰፊው እንዳሰፈሩት በሱማሌ ክልል ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንደሚፈፀም በመግለፅ ለመጪው ምርጫ የሚሆናቸውን ድጋፍ ከፕሮጀክቱ ይፈልጋሉ። ፕሮጀክቱ በአፍሪካ አገሮች ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ፣ በንፁሃን ዜጎች ላይ ጥቃት እንዳይደርስ መከላከል፣ አጥፊዎችን መቅጣትና የጅምላ ጭፍጨፋዎችን የመከላከል ዓላማ አለኝ ቢልም ዋናው ቅኝቱ ግን እንብላው የሚል ነው። በአካባቢው የአሜሪካንን ጥቅም ከማስከበር ውጭ ሌላ ራዕይ የለውም።

የኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ ከአንድ ዓመት በፊት በሱማሌ ክልል ከዳርፉር ያልተናነሰ ጥፋት እየደረሰ እንደሆነ፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች የተባለ ተቋምም ሲያራግበው የነበሩትን ይህን ውል አልባ ውንጀላ ሴኔተር ፋይንጎልድ ረቂቅ ሕጉ ውስጥ በማካተት የሱማሌ ክልልን የኢነፍ ፕሮጀክት አጀንዳ ለማድረግ በገፀ-በረከትነት ማቅረብ ይፈልጋሉ። ይህ ፕሮጀክት እስካሁን በሱዳን፣ በቻድ፣ በሱማሊያና ምሥራቃዊ ኮንጎ የሚያካሂደውን በሰብዓዊ መብት የተለበጠ ጣልቃ ገብነት ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት የነዳጅ ቁፋሮ ኩባንያዎችን የፋይናንስ ድጋፍ የማግኘት ፍላጎት ውጤት ነው የሴኔቱ ክስ።

ሴናተሩ በኢትዮጵያ መንግስትና በአልኢትሃድ መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት እንዲሁም ከኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር ጋር እየተደረገ ያለው ድርድር የሱማሌ ክልልን ከቢቢሲ፣ አልጀዚራ እና ኒውዮርክ ታይምስ ጦር አውርድ ዘገባ እንዳያስቀረው የፈለጉም ያስመስላቸዋል። አለበለዚያ በክልሉ እስካሁን ስለተሰራው መንገድ፣ ሆስፒታሎች፣ አውሮፕላን ማረፊያ ወዘተ... መናገር ይቅርና በአካባቢው ስለተፈጠረው ሰላም እንዴት አንዲት ቃል እንኳ አይጠቅሱም ? ይህ ለራሳቸው ያላቸውን ተዓማኒነት(Integrity) እንድንጠራጠር ያደርጋል። ለነገሩ ስለሱማሌ ክልል የሴኔተር ፋይንጎልድ ቡራኬን ልንጠብቅ አይገባም። የኢትዮጵያ ህዝቦች እጣ ፈንታቸውን አሳልፈው አለመስጠታቸው የማይዋጥላቸው ኃይሎች (ይህ ጥላን የመጠርጠር አባዜ አይደለም) ገፅታችንን የሚያጎድፍ መግለጫ ከማውጣት እና ረቂቅ ሕግጋትን ወደፊትም ከማውጣት አይቦዝኑም። ከአንድ አመት በፊት በወጣው መግለጫ ኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ የ2002 ምርጫ ቀውስ ሊስከትል እንደሚችል ቢወተውትም ሟርቱ አልሰመረለትም። ስለሆነም እንደዚሁ አይነት መግለጫ በማውጣት ህዝቡም መንግስትም ተረጋግተናል ብለው እንዳይቀመጥና የእነሱ ተላላኪ እንዲሆን በማድረግ የመደራደር አቅሙን መቀነስ ዓላማቸው ነውና። ስለሆነም በአገራችን በኩል ለዚህ የሚመጥን ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። አሁን በአንፃራዊነት አንድ አይነት አገራዊ የመግባባት መንፈስ እየሰፈነ ነው። ህዝቡም አዲስ ተስፋን ሰንቋልና እንደ አንድ ህዝብ በመንቀሳቀስ አንገት

የሚያስደፋንን ድህነት ታሪክ የማድረግ ኃላፊነት አለብን። ከአሜሪካ ጋር የምናደርገው ግንኙነት ከበርካታ ልዩነቶቻችን ጋር በሁለቱም አገሮች ጥቅም ላይ የተመሠረተ ነው። በየትኛውም ሴናተር ቢል ስለቀረበ የሚቀየርም አይደለም። ስለሆነም እንዲህ አይነት ቢል ሲወጣ ብልሃትና ብስለት በተላበሰ የተቀናጀ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ማምከን ይጠበቃል። ዞሮ ዞሮ አሜሪካም አሜሪካ፣ ኢትዮጵያም ኢትዮጵያ ናት። መልካም አዲስ ዓመት። ሠላም።